የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ትብብር - ዴሞክራሲያዊ ምትሕብባር ትግራይ
TIGRIAN ALLIANCE FOR NATIONAL DEMOCRACY (TAND)
e-mail: czanareg@hotmail.com

# ኢትዮጵያዊነት ስሜት ለሌለው ስለኢትዮጵያ የሚነገረው ሁሉ “ማደንዘዣ” ቢሆንበት ምን ያስገርማል!

የህወሓት ተሃድሶ ማእከላዊ ኮሚቴ አባልና በድርጅቱ ውስጥ የፈለጉትን ውሳኔ የማስወሰን ጉልበት እንዳላቸው የሚታመነው አቶ ስብሓት ነጋ የድርጅታቸው ንብረት ከሆነው ድምጺ ወያኔ ጋር ያደረጉትን ቃለ ምልልስ በጥንቃቄ ተከታትለነዋል።

የአቶ ስብሐት ቃለ ምልልስ ድርጅታቸው ህወሓት ተሓድሶ በኢትዮጵያዊነት ላይ ያለው አቋም ምን እንደሚመስል ግልጥልጥ አድርጎ አስቀምጦልናል። አቶ ስብሓትና ግብረ-አበሮቻቸው በኢትዮጵያዊነት ላይ የነበራቸውና ያላቸው አቋም ምን እንደሆነ ቀድሞውኑም ጠንቅቀን የምናውቀውና ያስተጋባነው ቢሆንም፣ ዛሬ በራሳቸው አንደበት በይፋ የእምነት ቃላቸው ሰጥተውበታል። በአቶ መለስ ዜናዊ በ1979 ዓ.ም ስለ ኤርትራ የተደረሱ “ቃልሲ ህዝቢ ኤርትራ እንካበይ ናበይ” (የኤርትራ ህዝብ ትግል ከየት ወዴት)ና “ብረት ህዝቢ ኤርትራ ቁልቁል አፉ ኣይድፋእን” (የኤርትራ ህዝብ የጠመንጃ አፈሙዝ ቁልቁል አፉ አይደፋም) የሚሉ ሁለት መጻሕፍቶችም የሚያስረዱን ይህንን ዛሬ በአቶ ስብሐት ነጋ የተነገረንን ሀቅ ነው። ስለሆነም በቃለ ምልልሱ ውስጥ የተገለጸውን የህወሓት ተሀድሶ አቋም አጥብቀን የምንኮንነው ብቻ ሳይሆን አምርረን የታገልነውና የምንታገለው ቢሆንም አቶ ስብሓት ነጋ በራሳቸው አንደበት እውነቱን ግልጽልጽ አድርገው በማቅረባቸው ህዝቡ እውነተኛ ግንዛቤ እንዲያገኝ ስለሚረዳ ሳናመሰግናቸው አናልፍም። ከአቶ ስብሐት ቃለ-መጠይቅ እንደምንረዳው የህወሓት ተሓድሶ/ኢህአዴግ መሪዎች መሠረታዊ ችግር የሚጀምረው በኢትዮጵያዊነት ላይ ካላቸው እምነት ነው። አቶ ስብሓት “በአፄ ኃይለሥላሴና በከፊልም በደርግ” ስለ ኢትዮጵያ ታላቅነት ይነገር የነበረውን “ማደንዘዣ (አንስቴዥያ)” በማለት እንደሚከተለው በማለት አብጠለጥለውታል። ይኸውም “……የኢትዮጵያ ህዝብን የመሰለ የለም፣ ኢትዮጵያን የመሰለ አገርም የለም። እምቅ ሀብት፣ ድንግል መሬት፣ ጨዋ ህዝብ የሚል ካለህበት የማያንቀሳቅስ ችግርህን ለማየት የማያስችል፣ ማደንዘዣ፣ አንስተዥያ ምን ያህል እንደጎዳን፣ ምን ያህልም ኋላ ቀር እንዳደረገን የምናውቀው ነው። …..” በዚህ አገላለጻቸው አቶ ስብሐትም ሆነ ድርጅታቸው ስለ ኢትዮጵያ ታላቅነት የሚነገረው ሁሉ እንደማደንዘዣ እንደሚቆጥሩት ግልጽ ባለ ቋንቋ፣ በማያሻማ መንገድ ነግረውናል።

ስለሚገዛው አገር የሚነገርው መልካም ነገር ሁሉ እንደ “ማደንዘዣ” የሚቆጥር መሪ ምን ዓይነት ሀገራዊ ፍቅር ሊኖረው እንደሚችል፣ ምን ዓይነት መጪ አገር ተረካቢ ትውልድ ማፍራት እንደሚችልና ለሚገዛት አገር የሚያበረክተው አስተዋፅኦ ምን ሊሆን እንደሚችል ለህዝባችን ፍርድ የምንተወው ይሆናል። እንዲህ ዓይነት መሪ ላገር የሚኖረው ታማኝነት ምን እንደሆነ ሁሉም የሚገነዘበው ከመሆኑም በላይ በተግባርም ባገር ላይ ክህደት ሲፈጽሙ አይተናል። በበኩላችን መልካም መፈክር በመልካም ተግባር መደገፍ እንዳለበት ብናምንም፣ የኢትዮጵያ መሬት እምቅ ሀብት በከርሰ ምድር መያዙ፣ ሀገራዊ ሀብታችን በተለያዩ ምክንያቶች በጥቅም ላይ ባይውልም ድንግል መሬት እንዳለን መገለፁ፣ የኢትዮጵያ ህዝብ ጨዋ ህዝብ ነው ተብሎ መገለፁ የምንደግፈው የምናምንበትና ራሳችንም በአንደበታችን የምንናገረው፣ እውንነቱንም ለማሳየት አበክረን

የምንሰራበት ተስፋችን እንጂ “ማደንዘዣችን” አይደለም ብለን ከልብ እናምናለን። አቶ ስብሐት ያለፉት ሥርዓቶች ከመፈክር ያለፈ የሠሩት ነገር የለም እያሉን ነው። ያለፉት ሥርዓቶች የራሳቸው የሆኑ ጠንካራና ደካማ ጎኖች የነበሩዋቸው ቢሆንም ዛሬ የህወሓት ተሀድሶ/ኢህአዴግ ከሃዲ መሪዎችም ጭምር እንዲዘባነኑባት መስዋእትነት ከፍለው አንድነቷን አስጠብቀው አስረክበውናል። አቶ ስብሐትና ግብረ-አበሮቻቸው ግን እነዛ መሪዎች በኢትዮጵያ ህዝቦች መስዋእትነት ያቆዩዋትን አገር በቅጥረኝነት ተሰልፈው በማፈራረስ ላይ ይገኛሉ። ስለሆነም ተግባርና መፈክር አልተጣጣመም የሚለውን በመሠረተ ሐሳብ ደረጃ የምንጋራው ቢሆንም እንደ አቶ ስብሐት ስለ አገራችንና ህዝባችን ባለፉት መሪዎች የተነገረው መልካም ገፅታ ግን አንቅቶን እንጂ አደንዝዞን አያውቅም። እንዲያውም በተቃራኒው እንኮራበታለን።

ለዚህም ነው እነ አቶ ስብሐት ኢትዮጵያ ውስጥ የሥልጣን ቁንጮ ላይ የመቀመጥ መብት ሊነፈጋቸው ይገባል የምንለው። ኢትዮጵያን የሚያስተዳድር ፓርቲ ቅድሚያ ኢትዮጵያንና የኢትዮጵያን ክብር ማመንና መቀበል ይኖርበታል። አቶ ስብሐትና ግብረ-አበሮቻቸው ግን በማያሻማ ቋንቋ እንደ ነገሩን በልቦናቸው የኢትዮጵያዊነት መንፈስ የለም። ኢትዮጵያዊነትን ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ ያልተቀበለ ድርጅትም ሆነ ግለሰብም ኢትዮጵያን የማስተዳደር መብት ሊኖረው ፈፅሞ አይገባም።

ስለሆነም የአቶ ስብሐት ቃለ ምልልሰ መሠረታዊ ችግር የሚጀምረው በኢትዮጵያዊነት ላይ ካለቸው አቋም ነው። ኢትዮጵያዊነታቸውን ፍቀው ጥለዋል። በመሆኑም ስለ ኢትዮጵያ የሚወራው ሁሉ “ማደንዘዣ” ሆኖባቸዋል። እንዲህ ዓይነት እምነት ካለው ድርጅት ደግሞ የጠራና የነጠረ ኢትዮጵያዊነት መጠበቅ አይቻልም። የሚገዛውን ህዝብና አገር እንደ ራሱ ህዝብና አገር አድርጎ የማይቆጥር፣ የማይመካበትና የማይኮራበት ድርጅት የሌላ ባለ ጥቅም ተላላኪና ቅጥረኛ ከመሆን ሊያልፍ አይችልም። አቶ ስብሐት “ሻዓቢያ እንደ ተላላኪ ወይም የእህል ሸማች አድርጎ ያየን ነበር” ሲሉ የገለጹትም መሠረቱ ያለው እዚህ ላይ መሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም። አዎ! ሻዓቢያ ብሔራዊ ጥቅሙን አሳልፎ የሚሰጥ፣ የራሱን የማያከብር ጅላ ጅል ሲያጋጥመው መጠቀምያ ሊያደርገው፣ ጌታ ሊሆንበት መጣሩ የሻዓቢያን ብልጣብልጥነትና የህወሓትን ጅላ ጅልነት ያሳያል። (በጅልነት ነው እንኳ ቢባል)።

እውነቱ ግን ከአቶ ስብሐት ቃለ ምልልስ የተረዳነው ከዚህ የባሰ ነው። አቶ ስብሐትና አጋሮቻቸው ስለ ኢትዮጵያ የሚነገረው መልካም ነገር ካደነዘዛቸው፣ ቢወለዱባትም የኢትዮጵያዊነት ስሜት እንደሌላቸውና እንዳልነበራቸው በገሀድ ታይቷል። ይህ ደግሞ የትግራይን ህዝብ ቋንቋ እየተናገሩ የወጣላቸው ቅጥረኞች ሆነው ለመውጣት እንዳስቻላቸው በግልፅ ነግረውናል።

አቶ ስብሐት ህወሓት ከማነኛውም የኤርትራ ድርጅት በላይ ለኤርትራ ነፃነት እንደታገለ አስረግጠው ነግረውናል። “የኤርትራ ድርጅቶች ከደርግ ጋር በመደራደር የኤርትራን የነፃነት ጥያቄ ለሽምግልና አቅርበውት ነበር። የኤርትራን ነፃነት የማይቀበሉ ያልተደራጁ ኤርትራዊያን ግለሰቦችም ነበሩ። ህወሓት ግን በኤርትራ ነፃነት ላይ በወሰደው ፅኑ አቋም ምክንያት ብዙ ኪሳራ ቢደርስበትም ከማነኛውም የኤርትራ ድርጅት በላይ ለኤርትራ ነፃነት ታግሏል” በማለትም ይገልፁታል። እዚህ ላይም ቢሆን በግልፅ በራሳቸው አንደበት ከመነገሩ ውጭ የማናውቀው አዲስ ነገር የለበትም። ለኤርትራ ነፃነት ከኤርትራ ድርጅቶች በላይ መታገልና የኢትዮጵያ ህዝብ ልጆች ላይም እንዲህ ዓይነት ደባ መፈፀሙ ብዙዎቻችን ቀደም ብለን የምናውቀው ቢሆንም ሲነገራቸው የማያምኑ ወገኖች ነበሩ/አሉና ይኸው መርዶው ደርሶዋቸዋል፣ አቋማቸውን ለማስተካከልም ዕድሉ ተፈጥሮላቸዋልና እንዲያስተካክሉ እንመክራለን።

አቶ ስብሐት የህወሓት መሪዎች ለኤርትራ ነፃነት የከፈሉት ተጋድሎን አስመልክተው የሰጡት ቃለ ምልልስ በድምፂ ወያኔ ሬዲዮ ድረ-ገጽ ስለሚገኝ እዚህ መዘርዘሩ አስፈላጊ መስሎ አልታየንም። ዋና መሠረተ-ሐሳቡ የህወሓት ተህድሶ መሪዎች ለኢትዮጵያዊነት አደረግን ያሉት ትግል ኤርትራን ነፃ ለማውጣት የትግራይ ወጣቶችን ለመማገድ የተጠቀሙበት ስልት እንደነበረ ዛሬ በቃለ ምልልስ መልክ በገሀድ የተነገረን ቢሆንም፣ አጠቃላይ የህወሓት ተህድሶ መሪዎችና የሻዓቢያ መሪዎች ግንኙነት እስከ መጨረሻ ድረስ ለተከታተለው፣ የህወሓት ተህድሶ መሪዎች ዓላማ በኢትዮጵያ ልጆች መስዋእትነት ኤርትራን ነፃ ለማውጣትና ለመጥቀም ያከናወኑት የቅጥረኝነት ተግባር ምን ያህል አሳፋሪ እንደ ሆነ ለመገንዘብ አስችለዋቸዋል ብለን ከልብ እናምናለን።

በመሆኑም አቶ ስብሐት የነገሩን ሚስጢር ሳይሆን በገሀድ ያየነውና የመሰከርነው ነው። አቶ ስብሐትና ግብረ-አበሮቻቸው ኢትዮጵያ የሚል ስም ያደነዘዛቸው ለኢትዮጵያ ጥቅም ከመቆም ይልቅ ለኤርትራ ጥቅም መቆምን የመረጡ ለመሆናቸውና ከምንም በላይ የኤርትራን ጥቅም የማስከበር ተልእኮ እንደሚያስቀድሙ በተደጋጋሚ በተግባር አስመስክረዋል። የኤርትራ ድርጅቶች ችግሩን በሰላምና በኢትዮጵያ አንድነት ዙርያ ለመፍታት ከደርግ ጋር ሲያደርጉት የነበረ ድርድር እጅጉን እንዳንገበገባቸውና አምርረውም እንደተቃወሙት በዝርዝር አስረድተውናል። እዚህ ላይ ከህወሓት ተህድሶ መሪዎች ይልቅ፣ ለኤርትራ ነፃነት ፕሮግራም ነድፈው ኤርትራዊውን አሰባስበው ሲታገሉ የነበሩ ድርጅቶች (ሻዓቢያና ጀብሀ) የበለጠ የኢትዮጵያዊነት ስሜት እንደነበራቸው ለመገንዘብ የሚያስችለን ሚስጢር መኖሩ ሊሰመርበት ይገባል። ይህም "እኖአ ሓዲጋስ ሓፍትኖአ ትናፍቕ" (እናቷን ትታ አክስቷን ትናፍቃለች) የሚለውን የትግርኛ ቢህል እንድናስታውስ ያደርገናል። የህወሓት ተህድሶ መሪዎች እውነት እውስጣቸው ኢትዮጵያዊነት ቢኖር ኖሮ መጀመርያ መጨነቅ የሚገባቸው ለእናት ኢትዮጵያ እንጂ ለኤርትራ መሆን አልነበረበትም። ኢትዮጵያዊነትን ክደው ቅጥረኝነትን የመምረጣቸው ሀቅ ግን በአንደበታቸው ነግረውናል። ይህንን ሀቅ በመረጃ አስደግፎ ለማሳየት ከዚህ ቀጥለን አንዳንድ የህወሓት ተህድሶ መሪዎች በተከታታይ ያተገበሯቸውን ተጨባጭ ክንዋኔዎችን ብናስቀምጥ አንባቢ ፍርድ እንዲሰጥ ይረዳል ብለን እናምናለን።

የህወሓት መሪዎች የኢህአዴግነት ካባ ለብሰው አዲስ አበባ በመግባት ከመረጡዋቸው ወገኖች ጋር በመሆን የሽግግር መንግሥት ሲመሠርቱ የህዝብ ውክልና አልነበራቸውም። ቢሆንም ለኤርትራ ነፃነት ከማንም በፊት እውቅና ከመሥጠትና ምንም ዓይነት ለሬፈረንደም የሚመች የተሟላ ቅድመ-ሁኔታ ባልተፈጠረበት በሬፈረንደም ስም የኤርትራን ህዝብ ለአንድ ጥቅሙን ለማያስከብርለት አምባገነን ድርጅት አሳልፈው መስጠታቸው ይታወቃል። በዚህ ወቅት ዘላቂ የኢትዮጵያ ጥቅሞች ላይ በማሴር ተባብሪ ሆነው እያወቁ አሳልፈው ሰጥቷል።

ሻዓቢያ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ላይ እንደፈለገ እንዲጨፍር ተደርጎ የነበረው ሙሉ የህወሓት መሪዎች ትብብርና ተሳትፎ ስለ ነበረበት መሆኑ የምንስተው አይደለም። የኢህአዴግ መሪዎች በኢትዮጵያ ሞት ኤርትራ እንድትፋፋ የሠሩበትና የተባበሩበት መሠረታዊ ምክንያት ከኢትዮጵያ ይልቅ ለኤርትራ የገቡት ቃልኪዳን በልጠባቸው ነው።

በባድመ ሰበብ ተጀምሮ የብዙ ሺ ወገኖቻችን ሕይወት የበላው ጦርነት በኢትዮጵያ ልጆች ደም የጦር ሜዳው ውሎ በአሸናፊነት እንደተጠናቀቀ አልጀርስ ድረስ በመንዝ የክህደት ሰነድ ፈርመው ሄግ ላይ በልጆቿ ደም የተከበረውን የኢትዮጵያ መሬት

(አንዳንዱ ቦታም ፍርድ ቤቱ የኢትዮጵያ ነው ሲል እኛ አልጠየቅንም በማለት) ለኤርትራ በማስረከብ "አሸንፈናል" በማለት ሊያሞኙን ሞክረው በኢትዮጵያ ልጆች ቆራጥነት ቢያንስ ጊዜ እስኪገዙ ድረስ ከሽፎባቸዋል።

ኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና የፍትሕ መዛባት በብሔራዊ እርቅ ይፈታ ተብሎ ለሚቀርበው ህዝባዊ ጥያቄ የተጣላ የለም እያሉ ሲያፌዙ፣ ከሻዕቢያ ጋር ግን እንታረቅ እያሉ ደጅ በመጥናት ላይ ይገኛሉ። በኛ እምነት የውጭ ጠላትን ለመመከት የሚቻለው አስቀድሞ የውስጥ ቅራኔን በመፍታት እንደ አገርና ህዝብ ተወሃህደን፣ በልጽገን፣ በውስጣችን ተጠናክረን ስንገኝ ነው። የውስጥን ቅራኔ አስቀድሞ መፍታት ከሁሉም በፊት ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው የምንለውም በዚህ ምክንያት ነው።

ገና በትግል ወቅት የኤርትራ ቅኝ ግዛትነት ጥያቄ አይዋጥልንም ያሉ ኢትዮጵያውያን ታጋዮች በህወሓት መሪዎች መጥፋታቸውና ሌላው ጥያቄውን እንዳያነሳ መማሪያ መደረጋቸው ይታወቃል። ለምን የሚል ጥያቄ ቢነሳ የህወሓት ተሀድሶ መሪዎች ያጠለቁት ኢትዮጵያዊ ጭንብል ተገልጦ የክህደት ሴራቸው እንዳይጋለጥ በመፍራት መሆኑ ግልጽ ነው።

አቶ ስብሐት ዛሬም ቢሆን የኤርትራ ነፃነትን ለመጋፋት የሚነሳ ማነኛውም ኃይል ከማጥፋት ኢህአዴግ ወደ ኋላ ይላል ብለው እንደማያምኑ ያስረዳሉ። ከዚህ አባባል ውስጥ ሁለት መሠረታዊ ነገሮችን መገንዘብ ይቻላል። መልእክታቸው ቀላልና ግልጽ ነው። አብዛኛው የኢትዮጵያን አንድነት ተቀብሎ የተደራጀ ኢትዮጵያዊ ተቃዋሚ ድርጅት የኤርትራ መገንጠል ሕጋዊ ነው ብሎ አያምንም። በአሁኑ ሰዓት ሌላ የውጭ ኃይል ኤርትራን ይተናኮሳል ተብሎ የሚገመት የለም። በመሆኑም የነ አቶ ስብሓትና መለስ ፍራቻ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ሥልጣን ከጨበጠ የኤርትራ ነፃነት አደጋ ሊገጥመው ይችላል የሚል ፍርሐት እንዳላቸው ያሳያል። ሁለተኛም የኤርትራ ህዝብ ኢትዮጵያዊነቱን ለማረጋገጥ እንቅስቃሴ ቢጀምር ቀዳሚ መቺ ኃይል የህወሓት ተሀድሶ መሪዎች ኃይል እንደሆነ እየተነገረን መሆኑ ነው። ስለሆነም የኤርትራ ነፃነት ላይ ጥያቄ ምልክት ያለው ኢትዮጵያዊ ድርጅት ኢትዮጵያ ውስጥ ሥልጣን ላይ እንዲመጣ ብቻ ሳይሆን የፖለቲካ እንቅስቃሴ እንዲያደርግም አይፈቅዱም። ወደ ሥልጣን የሚመጣበት አጋጣሚ ከተፈጠረም እንዴት እንደሚመቱት በግልጽ አሳይተውናል። በዚህም የህወሓት ተሀድሶ/ኢህአዴግ መሪዎች በአፍቃሬ ኤርትራነት የታወሩ መሆናቸው ለማየት ይቻላል። ያልተደራጁ የኤርትራ ነፃነትን የሚቃወሙ ኤርትራውያንንም ታግለናቸዋል ማለታቸው የሚያመለክተውም ይህን ሀቅ ነው። ከነዚህ ሁሉ ጭብጦች የህወሓት ተሀድሶ መሪዎች በውስጣቸው ቅንጣት ታክል የኢትዮጵያዊነት ስሜት እንደሌላቸው ያስረዳል።

ከዚህም ሌላ አቶ ስብሐት ነጋ ሲቪሊቲ ከተባለው የኢህአዴግ የኤሌክትሮኒክስ የውይይት ክፍል ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ "አሁን ያለው ሕገ-መንግሥት ቢነካ ትግራይ አውቶማቲካሊ ይገነጠላል" በማለት የተናገሩት አሳፋሪና የተለመደ የአምባገነኖች የማስፈራርያ ቀረርቶ ነው። እንዲያው አምባገነኖች ሥልጣን ላይ የሚኖሩት በከፋፍለህ ግዛና በእኔ አውቅልሀለሁ እንደሆነ ይታወቃል። ይህ የአምባገነኖች የጋራ ባህሪ ነው። አቶ ስብሐት በዚህ አባባላቸው ለትግራይ ህዝብ ያላቸው ንቀት ምን ያህል የጠለቀ እንደሆነ በማያሻማ መንገድ አሳይቷል። ያላወቁት ነገር ቢኖር ተግባርና ምኞት ለየቅል መሆኑን ነው። ኢትዮጵያ ከራሷ ትገነጠላለች የሚለው አስተሳሰብ ክህደት ከተጠናወታቸው አምባገነኖች እንጂ ከጤነኛ ጭንቅላት የሚመነጭ አይደለም። ሁሉም ነገር የራሱ ልክ እንዳለው አቶ ስብሐትና ግብረ-አበሮቻቸውም የራሳቸው የሆነ ልክ

እንዳላቸው የተረዱት አይመስሉም። የትግራይ ህዝብ ኢትዮጵያ እንዳትፈራርስ ተገቢ መስዋእትነት እየከፈለ የኖረ ህዝብ እንጂ በአቶ ስብሐት ትእዛዝ ኢትዮጵያዊነቱን የሚክድ ህዝብ አይደለም። በነ አቶ ስብሐትና ግብረ-አበሮቻቸው ሓሳብን በነፃ የማንሸራሸር መብት ተነፍጎት የኢትዮጵያ ዴሞክራቶች ያላቸው አመለካከትና ኢትዮጵያዊ ራእይ እንዳይሰማና እንዳያነብ በማድረግ የተወሰኑ ፅንፈኞች የሚያራምዱት የጥላቻ ፖለቲካ እያራገቡ ለጊዜውም ቢሆን በማደናገር እንዳይነሳባቸው ስላደረጉ፣ በፈለጉበት ጊዜ በእጅ ጥምዘዛ መገንጠል አለብህ ብለው ሊያስገነጥሉት እንደማይችሉ የገባቸው አይመስልም። አቶ ስብሐት! ሁሉም ልክ አለው። ዕድሜ ለነዛ ለጥላቻ ፖለቲካ አቀንቃኝ ጽንፈኞች ይበሉ። ባይሆን ኖሮ የርሱዎና የግብረ-አበሮችዎ ሴራ ገና ድሮ ልክ ገብቶ እንደነበረ የሚስቱት አይሆንም። ወዮልዎ! የትግራን ህዝብ ኢትዮጵያዊነት እፈታተናለሁ ያሉ ዕለት። ዳሩ እርሱዎም ሆኑ ግብረ-አበሮችዎ ምላሹን ጠንቅቃቹህ ታውቁታላቹ። የትግራይን ህዝብ ኢትዮጵያዊነት ሊፈታተን የሚችል ከሰማይ በታች ኃይል አለ ብለን አናምንም። በተለይ ደግሞ ኢትዮጵያዊነት የራሱዎን ቃል ብንጠቀም እንደ "ማደንዘዣ" "አንሰቴዢያ" የሚሰማው እንደርስዎ ያለ ሰው የትግራይን ህዝብ ለማስገንጠል አይችልም። ውጤቱን ስለሚያውቁት እንዲያው ለጉራና ለማስፈራርያ በተቆጣጠሩት መገናኛ ብዙኃን ይናገሩት እንጂ የትግራይ ህዝብ ፊት ቀርበው አይደግሙትም። እውነቱን ለመናገርም ይህንን ባለ ማድረግዎ ፈሪ አንልዎትም፣ መፈራት በሚገባበት ቦታ ላይ ሁሉም መፍራት አለበትና። እርስዎም ይህንን እንደሚያውቁ እናውቃለን። ዛሬ ምን ተማምነው ይህንን ህቅ ገህድ ለማድረግ እንደፈለጉ ባናውቅም፣ እስከ ዛሬ ድረስ ማንነትዎን ደብቀው የትግራይ ህዝብ ቋንቋ እየተናገሩ በውስጥ አርበኝነት አድብተው የቆዩበት ምክንያትም የጠቀስነው ፍርሀት ነው። ስለዚህ ያውቁታል።

እዚህ ላይ ስለ አንድ ሌላ የወቅቱ አንገብጋቢ ጉዳይ አጠር አርገን ማንሳት እንፈልጋለን። ይኸውም የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች ጉዳይ ነው።

ሰሞኑን ከግንቦት 1997 ዓ.ም ምርጫ ጋር በተያያዘ የቅንጅት መሪዎች፣ ጋዜጠኞችና የተለያዩ የሲቪክና የሲቪል ማኅበረ-ሰብ አባላት በግፍ በየእስር ቤቱ ተወርውረው የተወሰኑት ከኢህአዴግ ድርጅታዊ ፍርድ ቤት ፍትሕ ይገኝ ይመስል እየተመላለሱ ከቆዩ በኋላ፣ ይኸው ዛሬ በፖለቲካ ድርድር ሊፈቱ ነው ተብሎ እየተናፈሰ በመስማት ላይ ነን። ከመጀመርያውም መታሠር ያልነበረባቸው ናቸው ብለን ብናምንም፣ የሚናፈሰው ወሬ እውነት ሆኖ እነዚህ የሂልና እስረኞች ከእስር የሚወጡ ከሆነ በደስታ የምንቀበለው ነው። ቢሆንም ስጋት አለን። ስጋታችንም እነዚህ ሰዎች በሕግ ያለመታሰራቸውን ያህል አሁንም በዓለም አቀፍና በኢትዮጵያ ህዝብ ግፊት እንጂ በመብትና በሕግ እየተፈቱ ነው ብለን የምናምንበት ምንም መረጃ የለንም። ለዚህ ጥርጣሬአችን መሠረታዊ የሆነ ምክንያት አለን። በሺዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን የፖለቲካ እስረኞች አሉ። አብዛኞቹ የት እንደታሠሩም አይታወቅም። ሌላ ቀርቶ ኢህአዴግ ፍርድ ቤት ፊት እንኳ አልቀረቡም። ስለነዚህ ሺዎችና አሥር ሺዎች እንኳን ዓለም አቀፍ ኮሚኒቲ እኛ ኢትዮጵያዊያንም የሁሉም የምናውቀው ሙሉ በሙሉ ነው ብለን አናምንም። ኢህአዴግ ከእነዚህ ከግንቦት 1997 ዓ.ም ምርጫ ጋር በተያያዘ ከታሠሩት ውስጥ መታሰራቸው በዓለም አቀፍ ኮሚኒቲ የሚታወቁትን ተጽእኖ ስለበዛበት ፈታ ማለት የሕግ-ሥርዓት በአገራችን አለ ማለት እንዳልሆነ ግልጽ መሆን ይኖርበታል። ለዚህ የፍትሕ መዛባት ዋናው ተጠያቂ ኢህአዴግ ቢሆንም ለፍትሕ እንታገላለን የምንለው ወገኖችም የምናቀርበው ጥያቄ ሁሉ አቀፍ አለመሆኑ ያሳስበናል። ዛሬ ፍትሕ በቅንጅት ደጋፊ፣ በሥዩ አብራሀ ደጋፊ፣ በአበራ የማነአብ ደጋፊ፣ በፀጋዬ ገ/መድኅን ደጋፊ፣ ......ወዘተ ተለያይተን ፍትሕን ለሁሉም ሳይሆን ለምንደግፈው ወገን ብቻ እየጠየቅን ነው። በየወብ ሳይቱ የሚወጡ ፅሑፎችና በየፓል ቶክ ክፍሎች

የሚንፀባረቀው ይህ ሀቅ ነው። የበለጠና ዘላቂ ውጤት ሊገኝ የሚችለው ግን ሁላችንም በጋራ ፍትሕ ላጣ ፍትሕ ብለን ብንቆም ነው። የበለጠ የሚያምርብንና ፍሬም ማፍራት የሚቻለውም በዚህ መንገድ ብቻ ነው ብለን እናምናለን። በመሆኑም አሁን ይፈታሉ ስለሚባሉት እስረኞች ዜናው እውነት ከሆነ በመፈታታቸው ከፍተኛ ደስታ እንደሚሰማን እየገለጽን፣ ስለ አጠቃላይ የፍትሕ ሥርዓት ለሁሉም በእኩልነት መሰፍን የምናደርገው ትግል መቀናጀትና መወሃሃድ አለበት ብለን እናምናለን።

እንግዲህ ኢትዮጵያዊያን አገራችንን እየገዛ ያለ ኃይል ማን እንደ ሆነ ዛሬ ያ ኃይል ራሱ ማንነቱን ቁልጭ አድርጎ ነግሮናል። ይህ ኃይል ኢትዮጵያ የሚል ቃል ሲነሳ ለዚህች ውድ አገራችን ካለው ጥላቻ የተነሳ የሚደነዝዝ መሆኑ ራሱ ገልፆታል። በመሆኑም ሁሉም ዓይነት ፅንፈኝነት እየታገልን በአምባገነን ቡድኖች ሳይሆን በህዝባዊ ሕገ-መንግሥት የምትመራ ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመገንባት የምናደርገው ጥረት ከማንም ጊዜ በላይ አጠናክረን እንድንቀጥል ት.ዴ.ት ሀገራዊ ጥሪውን ያቀርባል።

የኢትዮጵያ ህልውና በጀግኖች ልጆቿ መስዋእትነት ይከበራል!!!
በከሃዲዎችና ቅጥረኞች መቃብር ላይ ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ትገነባለች!!!

ግንቦት 1999 ዓ.ም
ት.ዴ.ት